## መመሪያ ቁጥር 997/2016

# ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት መመሪያ 997/2016

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን

መጋቢት፣ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 997/2016

## ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት መመሪያ

የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ለሀገራችን አድማጭ ተመልካቾች በአማራጭነት የሚቀርቡበትን መንገድ በማመቻቸት የዜጎችን የመረጃ፣ የመዝናኛ እና የትምህርት ፍላጐት ማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ የተዘጋጁ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በሀገራችን ለሚገኙ አድማጭ ተመልካቾች በክፍያ የሚቀርቡበትን እና ዘርፉ በህግ የሚመራበትን አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 30 መሰረት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ሥራ ለመሠማራት የብሮድካስት ፈቃድ ማግኘት በማስፈለጉ እና የፈቃድ አሰጣጥ ሒደቱን ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ አሳታፊ እና ተደራሽ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(1)፣(5)፤ እና 31(1)(ሐ) መሰረት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ስራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልጉ አመልካቾች በመመሪያው የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ መስጠት፣ ዘርፉን ማስፋፋት፣ ለሕብረተሰቡ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ማመቻቸት እንዲሁም ባለፈቃዶች ሙያዊ ሥነ-ምግባርን፣ ሕገ መንግስቱን፣ የሀገሪቱን ሕጎች እንዲሁም የሕዝብን ሰላም፣ ደኅንነት፣ የዜጎችን ተነፃፃሪ መብቶች እና ጥቅሞች ባከበረ መልኩ በኃላፊነት ስሜት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 12(7) እና አንቀጽ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

# ***ክፍል አንድ***
# ***ጠቅላላ***

## *1. **አጭር ርዕስ***

***ይህ መመሪያ "ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 997/2016"*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## *2. **ትርጓሜ***

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ***"ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት"*** ማለት ትርፍ ለማግኘት በተቋቋመ በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው የንግድ ድርጅት ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ስራ ለመሰማራት ፈቃድ በተሰጠው አካል አማካኝነት የሚከናወን፤ በባለፈቃዱ እና አገልግሎቱን በሚገዙ ደንበኞች መካከል በሚደረግ ውል ወይም ግንኙነት መሰረት በውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን ማናቸውም የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ፈቃደኛ ለሆኑ ደንበኞች ለዚሁ አገልግሎት ከተዘጋጀ የመቀበያ መሳሪያ፣ ካርድ፣ ወይም የሚስጥር ቃል ጋር ለደንበኞች በክፍያ ሊቀርብ የሚችል የብሮድካስት አገልግሎት ሲሆን፤ በባለፈቃዱ የተዘጋጁ የፕሮግራም ቻናሎችን አይጨምርም፡፡ አገልግሎቱም በሳተላይት፣ በኬብል፣ ከምድር ወደ አየር ወይም በኢንተርኔት አማካኝነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

2/ ***"የፈቃድ አመልካች"*** ማለት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሰው ነው፡፡

3/ ***"ባለፈቃድ"*** ማለት በመገናኛ ብዙሃን አዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ ከባለሥልጣኑ የተሰጠው ሰው ሲሆን፤ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ይህንኑ አገልግሎት እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ባለፈቃድንም ይጨምራል፡፡

4/ ***"ፕሮግራም"*** ማለት ትኩረቱን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ጉዳይ ላይ ያደረገ በድምፅ፣ በምስል ወይም በድምፅና በምስል ተቀነባብሮ ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅ ወይም ለማዝናናት በውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ ተቀርጾ በውጭ ሀገር የተቀነባበረ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራምና የዜና ስርጭት ነው፡፡

5/ ***"የፕሮግራም ቻናል"*** ማለት የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ፕሮግራሞች በአንድነት ተቀነባብረው የሚቀርቡበት የራሱ መለያ ያለው ማሠራጫ ቻናል ነው፡፡

6/ ***"ቁጥጥር"*** ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች በሕግ መሠረት መሥራታቸውን የመከታተል፣ የመደገፍ፣ የማረጋገጥና የመቆጣጠር ሥራ ነው፡፡

7/ ***"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"*** ማለት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ተቀብሎ፤ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

8/ ***"የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ናቸው፡፡

9/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

10/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

11/ ***"አዋጅ"*** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

12/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ነው፡፡

13/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

14/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ የሴትንም ያካትታል፡፡

## *3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>*

ይህ መመሪያ፡-

ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በማናቸውም የማሰራጫ መንገድ አማካኝነት በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ በተሰጣቸው ባለፈቃዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## *4. <u>የመመሪያው መርሆች</u>*

1/ ለዜጎች አማራጭ የመረጃ፣ የትምህርትና፣ የመዝናኛ ምንጭ መፍጠር፡፡

2/ በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ አመልካቾች ፈቃድ በማግኘት የመሰማራት መብታቸውን ማረጋገጥ እና ዘርፉንም በሕግ መሰረት መቆጣጠር፡፡

3/ የፈቃድ አሰጣጥ ሒደትንና የፈቃድ መስፈርቶችን ግልፅ፣ ፍትሐዊና አሳታፊ ማድረግ እንዲሁም፤ የመገናኛ ብዙሀን ባለቤትነትን፣ የአገልግሎቱ ተጠቃሚነትን፤ የመረጃ ብዝሃነትና ስብጥርን የሚያሰፍን መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

4/ ባለፈቃዶች ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ ሆነው አገልግሎቱን ለደንበኞች መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡

5/ ባለፈቃዶች የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች መብትና ጥቅም በማክበር አገልግሎት መስጠታቸውን እንዲሁም የሙያውን ሥነ-ምግባር፣ ሕገ-መንግስቱንና የሀገሪቱን ሕጎች አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

6/ ሀገራዊ ፌጠራዎችን ማበረታታት እና የሀገር ውስጥ የቋንቋ ብዝሃነትን ማረጋገጥ

## 5. የባለቤትነት መብት

1/ የአክስዮን ድርሻው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘ እና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ሥራ የመሠማራትና ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

2/ 25 በመቶ የሆነ የአክስዮን ድርሻው በውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘ፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ሥራ ላይ የመሠማራትና ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

3/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አንድ የንግድ ድርጅት በድርጅቱ ባለቤትነት ሥር የሚተዳደሩ አንድ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ እንዲሁም አንድ የቴሌቪዥን፣ አንድ የሬዲዮ፣ አንድ የጋዜጣ፣ አንድ የመፅሔት እና አንድ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም ይችላል፡፡

## 6. ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ የማይሰጣቸው አካላት

የሚከተሉት አካላት ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

1/ አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ፣

2/ አመልካቹ ድርጅት ወይም የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች በሌላ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ ወይም መፅሄት ውስጥ ከ25 በመቶ በላይ የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ከሆነ፤

3/ አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲ ከሆነ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተፈጥሮ ያለው ድርጅት ከሆነ፤

4/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ከ25 በመቶ በላይ የአክስዮን ድርሻ ያለው ከሆነ፤

5/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል ከሆነ፤

6/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም ከፖለቲካ መብቶቹ የታገደ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው ባለአክስዮን ወይም የበላይ አመራር ከሆነ፤

7/ በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የውጪ ሀገር ዜጋ ወይም በውጭ ሀገር ዜጎች የተቋቋመ ድርጅት ከ25 በመቶ በላይ የአክስዮን ድርሻ ያለው ከሆነ፣

8/ አመልካቹ ድርጅት በውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በውጭ ሀገር ሕግ የተቋቋመ ከሆነ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት የፈቃድ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት

### 7. አጠቃላይ

1/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ለ) ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ ቢኖረውም በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀጽ 29 ከተዘረዘሩት የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ መንገዶች መካከል ቀደም ሲል ፈቃድ ካገኘበት የፈቃድ አይነት በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ ሌላ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

ሐ) ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ ያለው ባለፈቃድ የሀገሪቱን ባህል የሚያስተዋውቁ፣ መልካም ገጽታዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ፣ የወጣቶችን የፈጠራ አቅም ሊያበረታቱ የሚችሉ ሀገር ውስጥ የተዘጋጁ ፕሮግራሞችን ያለማስታወቂያ እንዲያሰራጭ ይበረታታል፡፡

2/ የፈቃድ አመልካቹ የባለሥልጣኑን ማስታወቂያ ሳይጠብቅ፣ ያለ ውድድር፣ በማንኛውም ጊዜ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ እንዲሠጠው ማመልከት ይችላል፡፡

3/ አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መስፈርቶችን ካሟላ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

4/ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍሉ፡-

ሀ) ማመልከቻዎችን ለመገምገም አስፈላጊ ነው የሚለውን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ አመልካቾችን ይጠይቃል፣ አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ ይሰጣል፣

ለ) አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡ አመልካቹ

በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃድ ካልተሰጠው ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማመልከት በ15 ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡ የበላይ ኃላፊው በተጠቀሰው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ አመልካቹ በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማመልከት ይችላል፡፡

## 8. *ስለፈቃድ የማመልከቻ ቅፅ*

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፣ የማመልከቻ ቅፆችንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ እንዲሞሉ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

ሀ) የአመልካቹ ወይም የድርጅቱ መጠሪያ ስምና አድራሻ፣

ለ) ድርጅቱ የተቋቋመበት አገር፣ የባለአክስዮኖቹ ስም፣ አድራሻ፣ የአክስዮን ድርሻ መጠንና ዜግነት፣

ሐ) ድርጅቱና የድርጅቱ ባለአክስዮኖች በሌላ ጋዜጣ፣ መፅሄት፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የበይነ-መረብ ድርጅት ያላቸው የአክስዮን ድርሻ መጠን፣

መ) በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱትን የፕሮግራም ቻናሎች ብዛት፣ ቋንቋ፣ የእያንዳንዱን ቻናል ስም፣ የይዘት አይነትና ትኩረት፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የፕሮግራም ቻናሎቹ የተዘጋጁበትን አገር፣ የቻናሎቹን አቅራቢ ባለቤት ስምና አድራሻ፣

ሠ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣

ረ) ከፕሮግራም ቻናል ባለቤቶች ጋር የተደረገ ውልና መሰል መረጃ ካለ፣

ሰ) አመልካቹ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ሥራ ላይ የነበረ ከሆነ የደንበኞቹን ብዛት፣

ሸ) የሚጠቀምበትን የሳተላይት መጠሪያ ስም፣ የሳተላይት አከራዩ ወይም ባለቤት ወይም ሌላ ማሰራጫ ባለቤት ስም፣ አድራሻ፣ የተደረገ ውልና መሰል መረጃ ካለ፣

ቀ) ባለፈቃዱ አገልግሎቱን ለደንበኞቹ የሚያደርስበትን ዘዴ እና ለስርጭቱ የሚውለውን የቴክኖሎጂና የመሣሪያ አይነት ካለ፣

በ) አገልግሎቱ የሚሰጥበትን፣ የማሰራጫ መሳሪያው የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን ቦታ ካለ፣

ተ) ስርጭቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሸፍነው አካባቢ፣

ቸ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገው የገንዘብና የካፒታል መጠን፡፡

ነ) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፣

## 9. *ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች*

1/ አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው መሆኑን የሚያስረዳ በሠነዶች አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠ የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የንግድ ምዝገባ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ለ) በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱትን የፕሮግራም ቻናሎች ብዛትና ቋንቋ፣ የእያንዳንዱን ቻናል ስም፣ የይዘት ትኩረት፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የፕሮግራም ቻናሎቹ የተዘጋጁበትን አገር፣ የቻናሎቹን አቅራቢ ባለቤት ስምና አድራሻ ማስረጃ፣

ሐ) አመልካቹ የፕሮግራም ቻናሎቹን ለደንበኞቹ ለማድረስ ከውጭ አገር የቻናል ባለቤት ወይም አቅራቢ ድርጅት ጋር ያደረገው የውል ወይም የስምምነት ሰነድ፣

መ) ከሳተላይት አገልግሎት ሰጪው ወይም ከማሰራጫው ባለቤት ጋር የተደረገ ማንኛውም አይነት ስምምነት ወይም ደብዳቤ ካለ፣

ሠ) የብሮድካስት አገልግሎትና የቴክኒክ ሁኔታን የሚገልፅ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣

ረ) ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ የገንዘብ አቅምና የቴክኒክ እቃዎች ምንጭ ማስረጃ፣

ሰ) የአመልካቹ ድርጅታዊ መዋቅር ሰነድ፣

ሸ) አገልግሎቱ የሚሰጥበት፣ የማሰራጫ መሳሪያ የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን አድራሻ ማስረጃ ካለ፡፡

2/ በኢንተርኔት አማካኝነት አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያመለክት አመልካች ላይ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1(መ) ከተደነገገው በስተቀር ንኡስ አንቀጹ ተፈጻሚ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተጨማሪ አመልካቹ አገልግሎቱን የሚሰጥበትን የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ አይነት የሚገልጽ ማስረጃ እና ከፕላትፎርሙ ባለቤት ጋር ያደረገውን ስምምነት ሰነድ፣

3) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ ሰነዶች፤

## *10. ማመልከቻን ስለማጣራት እና ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ*

1/ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍሉ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 እና አንቀፅ 9 የቀረበለትን ማመልከቻ እና ደጋፊ ሰነድ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ አመልካቹ፡-

ሀ) የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የንግድ ምዝገባ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ፣

ለ) የገንዘብ፣ የቴክኒክ እቃዎች አቅሙን እና ምንጩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሕጋዊ ማረጋገጫ ማስረጃ ካላቀረበ፣

ሐ) ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣

መ) በአዋጁ አንቀፅ 24(2)፣ 40 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሰረት ድርጅቱ ፈቃድ የማይሰጠው ሰው ከሆነ፤

ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ ማሳለፍ ሳያስፈልገው ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለፈ አመልካች ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ በመሸጋገር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የፈቃድ መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

## *11. የፈቃድ መስጫ አጠቃላይ መስፈርቶች*

1/ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካትታል፡፡

ሀ) ከብሮድካስት አገልግሎት የቴክኖሎጂ እድገት ጋር በተያያዘ ሊሰጥ ከታሰበው አገልግሎት የሚጠበቅ የቴክኒክ ጥራትና አመልካቹ በፕሮጀክት ጥናት ሠነዱ የዘረዘራቸው መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ካሉ አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

ለ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣ ድርጅታዊ ብቃት፣ የሥራ ልምድና ሙያዊ እውቀት፤

ሐ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ፣ አስተማማኝነትና ሥራውን ለማከናወን ያለው ዝግጁነት፤

መ) በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱት የፕሮግራም ቻናሎች ዓይነት፣ ብዛትና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶችና ከባህልና ከህግ ያልተቃረኑ መሆን፤

ሠ) ለአገር ውስጥ የፕሮግራም ቻናሎችና ለአገር በቀል ፕሮግራም፣ ይዘትና ሙዚቃ የሰጠው ትኩረት፣

ረ) በሕግ የሰውነት መብት በተሠጠው የንግድ ድርጅት አማካኝነት ከአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ከሚገኝ ክፍያ ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ፣ ከፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ ከመንግስትና ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የንግድ ድርጅት የተቋቋመ መሆኑ፣

2/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀፅ 32(1) መሰረት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ ተጨማሪ የፈቃድ መስፈርቶችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## *12. የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች እና የመገምገሚያ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት*

1/ የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በሕግ የሰውነት መብት በተሠጠው የንግድ ድርጅት አማካኝነት ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ ወይም ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ስራ ለመሰማራት ፈቃድ የተሰጠው መሆኑ፣ ከደንበኞች በሚሰባሰብ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ ወይም ከኮሚሽን ወይም ከመሰል ክፍያ ገቢ የሚተዳደር መሆኑና ከፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ ከመንግስትና ከልዩ ልዩ አካላት ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ መሆኑ፣

ለ) የድርጅቱ ባለአክስዮኖች ብዛትና ስብጥር፣

ሐ) አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው የገንዘብና የቴክኒክ እቃ የካፒታል አቅምና ምንጭ፣ የሰው ሀይልና የድርጅታዊ አቅም፣ ብቃት፣ ዕውቀትና የሥራ ልምድ፣

መ) በፕሮጀክት ሰነዱ የተዘረዘሩና ለስርጭቱ የሚውሉ የብሮድካስት መሣሪያዎች ካሉ አይነታቸው እና የቴክኒክ ደረጃና ብቃት፣

ሠ) አገልግሎቱ የሚሰጥበት ወይም የማሰራጫ መሳሪያ፣ የሚቋቋምበት ቦታ ካለ አስተማማኝነት፣

ረ) በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱት የፕሮግራም ቻናሎች ዓይነት፣ ብዛት፣ አላማና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኀበራዊ ፍላጎቶችና ለትምህርታዊ ፕሮግራሞች የሰጠው ትኩረት፣ ለህዝብ የሚኖረው ጠቀሜታና ከባህልና ከህግ ተቃራኒ አለመሆኑ፣

ሰ) ለሀገር ውስጥ የፕሮግራም ቻናሎችና ለሀገር በቀል ፕሮግራምና ሙዚቃ የሠጠው ትኩረት፣

ሸ) ከሕብረተሰቡ የቀረበ ተደጋጋሚ ቅሬታና ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ተደጋጋሚ የማስተካከያ ግብረመልስ አለመኖሩ፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 እና 12 የተዘረዘሩትን አጠቃላይና ዝርዝር የፈቃድ መስፈርቶች፤ እንዲሁም የተጠየቀውን የብሮድካስት ፈቃድ አይነት እና የማሰራጫ ቴክኖሎጂን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመልካቾችን ብቃት በመመዘን ነጥብ ለመስጠት የሚያስችለውን ዝርዝር የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት ሠነድ ያዘጋጃል፤ በባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማስፀደቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡

## 13. የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት

ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርአት ሂደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ አመልካቹ በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከደጋፊ ሠነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፡፡

2/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ፡-

ሀ) አመልካቹ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ በአንቀጽ 24(2)፣ 40 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል መሆኑን ካረጋገጠ፤ በዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልገው ማመልከቻውን ውድቅ እንዲሆንና ውሳኔው ለአመልካቹ በጽሁፍ እንዲገለፅለት የውሳኔ ሃሳቡን ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ለ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ማቅረቡንና ፈቃድ ሊሰጠው የሚችል አካል መሆኑን ካረጋገጠ፤ በአዋጁ አንቀጽ 37 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 12 የተዘረዘሩት የፈቃድ መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥና ለመመዘን ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ እንዲያልፍ ውጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

3/ የበላይ ሃላፊው ከፈቃድ ስራ ክፍሉ የቀረበለትን የአመልካቾች ሠነድና የውሳኔ ሃሳብ በመመርመር ወደ ሁለተኛ ማጣርያ ማለፍ የሚገባውን አመልካች በማፅደቅ ምዘና እንዲካሄድ ይወስናል፡፡

4/ የፈቃድ ስራ ክፍሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የቀረበለት ማመልከቻ በአንቀጽ 9፣ 11፣ እና 12 የተዘረዘሩትን ሰነዶችና መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ፤ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12(2) መሰረት በተዘጋጀው የፈቃድ አሰጣጥ የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ የአሰራር ሥነ-ሥርአት መሰረት የአመልካቹን ብቃት በመመዘን ውጤቱን የያዘ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በቀረበለት የፈቃድ ማመልከቻ ላይ አመልካቹም ሆነ ዜጎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ የበላይ ኃላፊው በፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት እንዲሁም በአመልካቹ የቀረበለትን ሠነድ፣ የሕዝብ አስተያየቱን ውጤትና ሌላ መረጃ መርምሮ አመልካቹ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋገጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ የወሰነውን ውሳኔ፣ ለውሳኔው ያደረሱ ምክንያቶችንና ፈቃድ ሲሰጥ ተግባራዊ የሚሆኑ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎችን ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ እንዲሁም በድረ-ገጹ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

8/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታን የያዘ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ከፈረመና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ ከከፈለ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

9/ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለፀለት አመልካች ደብዳቤ በደረሰው በ2 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈፀም እና በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታ ስምምነት ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ካልወሰደ የፈቃድ ውሣኔው ይሰረዛል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባለፈቃዱ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት

ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ የ3 ወር ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

11/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለንግድ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

12/ በዚህ አንቀፅ መሰረት በሳተላይት፣ በኬብል ወይም ከምድር ወደ አየር አማካኝነት ፕሮግራሞችን ተቀብሎ ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው እና በስራ ላይ የሚገኝ ሰው ይህንኑ አገልግሎት በኢንተርኔት አማካኝነት ለተጠቃሚዎች የሚያደርስ ከሆነ ሌላ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልገው ለባለሥልጣኑ በማሳወቅ ሲፈቀድለት በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ እንዳለው ሆኖ ይቆጠራል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረትም የሚተዳደር ይሆናል፡፡

## 14. *በፈቃድ አመልካች ላይ የሕዝብ አስተያየት ስለመጥራትና ለአመልካቹ ቃለመጠይቅ ስለማቅረብ*

1/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ለመገምገም የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰብ ከፍ ያለ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ለመጥራት ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማውጣት የብሮድካስት አገልግሎቱ በሚቋቋምበት አካባቢ ውስጥ የሕዝብ መድረክ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ አመልካቹ ፈቃድ በማግኘት አገልግሎቱን በጥራት ለማከናወን ያለውን ዝግጁነት በተመለከተ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎችና የፈቃድ ስራ ክፍሉ ለሚያቀርቡለት የቃል መጠይቅ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 15. *ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመንና የፈቃድ እድሳት*

1/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን 10 አመት ይሆናል፡፡

2/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተወሰነው የፈቃድ ዘመን ከማለቁ ከ1 ዓመት ባልበለጠና ከ6 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማሳደሻ ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን 1 አመት ይሆናል፤ ፈቃዱም በየአመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

4/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ፈቃዱን ከማደሱ በፊት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን፣ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች የተመለከቱ ግዴታዎች የማክበር የኋላ

ታሪክና የተወሰዱበት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አለመኖራቸውን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

ለ) ባለፈቃዱ በተገልጋዩ ሕብረተሰብ ተቀባይነትን ያገኘ፣ ተደጋጋሚ የሆነ የቅሬታ ሪከርድ የሌለበት፣ በባለሥልጣኑ የሞኒተሪንግና ክትትል ውጤት ተደጋጋሚ ግድፈት ያልተገኘበት መሆኑን፣ እና

ሐ) ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ አመታዊ ክፍያውን በወቅቱ ይከፍል የነበረ መሆኑን፤

በማረጋገጥ ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና መረጃዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ግዴታ የያዘ ስምምነት ሠነድ በመፈረምና ለፈቃድ እድሳት የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

7/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካች ጉድለቶቹ እስኪስተካከሉ ድረስ የፈቃድ ዘመኑ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ፈቃዱን ለ3 ወራት ባለሥልጣኑ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

8/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ላለማደስ የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ካመነ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ በመግለፅ በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ አስተያየቱን እንዲሰጥና ቅሬታ ካለው በፅሁፍ እንዲያቀርብ እድል ይሰጣል፡፡ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ምላሽ በመገምገም የአመልካቹን ፈቃድ የማያድስ ከሆነ ከ3 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

9/ ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቀርቦ የእድሳት ማመልከቻውን ሳያቀርብ የፈቃድ ማደሻ ጊዜው ካለፈ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ እንደተወ ተቆጥሮ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት መስጠትም አይችልም፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (9) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያላሳደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ፤ በዚህ መመሪያ የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

## 16. ለፈቃድ እድሳት የህዝብ አስተያየት ስለማሰባሰብ

1/ የበላይ ኃላፊው በአንቀጽ 15 የቀረበለትን የፈቃድ እድሳት የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የፈቃድ እድሳት ጥያቄ የቀረበለት መሆኑን ለህዝብ በመገናኛ ብዙሃን በማስታወቅ፤ የእድሳት

ማመልከቻውን በሚመለከት የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረክ ሊያዘጋጅ ወይም በጽሁፍ አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ አመልካቹ የቀረበውን አስተያየት በሚመለከት ባለስልጣኑ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሹን በጽሁፍ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 17. *ተቀባይነት ስላላገኘ የፈቃድ ጥያቄና የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ*

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13(2)(ሀ)፣ (6) እና (9) መሰረት የፈቃድ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ወይም ፈቃድ እንዳይሰጥ ወይም እንዲሰረዝ ከወሰነ፣ ማመልከቻው ውድቅ የሆነበትን ወይም ፈቃዱ የማይሰጥበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት በ14 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ፣ ወይም ሰፊ ስርጭት ባለው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15(5)፣(8) እና (9) መሰረት ፈቃዱን ላለማደስ ከወሰነ፣ ማመልከቻው ውድቅ የሆነበትን ወይም ፈቃዱ የማይታደስበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት በ14 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ፣ ወይም ሰፊ ስርጭት ባለው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

3/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

4/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

## 18. *የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች*

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) ለአመልካቹ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፣ ባለፈቃዱ ፈቃድ ለማግኘት ሲል በማመልከቻው የገለፀውን የፈቃድ ሁኔታ እና ባለፈቃዱ ሊከተለው የሚገባ ግዴታን መሠረት ያደረገ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ለ) ያዘጋጀውን የፈቃድ ሥምምነት ሰነድ አመልካቹ እንዲያገኘው፣ አስተያየቱን የመግለፅ እድል እንዲሰጠው እና የስምምነት ሠነዱን በመፈረም ፈቃድ እንዲሠጠው ያደርጋል፡፡

2/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው ላይ የገለፀው የፈቃድ ሁኔታና የፈቃድ ስምምነት ሠነድ የፈቃድ ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

3/ የፈቃዱ ሁኔታና ግዴታ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካትታል፡

ሀ) የፕሮግራም ቻናል ብዛትና ለውጥን፤

ለ) ስለቴክኒክ ሁኔታዎች፤

ሐ) ባለፈቃዱ ሥርጭት የሚጀምርበት ጊዜና ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

መ) የፈቃድና የእድሳት ክፍያ፤

ሠ) የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፤

ረ) የደንበኞች አጠቃላይ መረጃና የባለፈቃዱ የፋይናንስ ሪፖርት፤

ሰ) የፕሮግራም ቻናል ባለቤቶች አጠቃላይ መረጃ፤

ሸ) የፈቃድ ሁኔታዎች ሲጣሱ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች፤

ቀ ባለሥልጣኑ በመደበኛነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው የመረጃ አይነቶች፤

በ) ፈቃድ የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች፤ እና፣

ተ) ቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚያዙበትና እልባት የሚያገኙበት መንገድ፤ የሚሰጡ መፍትሔዎችና እርምቶች፤

ቸ) ስለአገልግሎትና የተጠቃሚዎች መብት የሚሰጥ መረጃ ግልፅነት፤

## ክፍል ሶስት
## ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች

### 19. የባለፈቃዱ መብቶች

1/ ባለፈቃዱ ተግባሩን በብቃት ለመፈጸም በሚያስችለው ሁኔታ በይዘት፣ በአደረጃጀትና በበጀት ከመንግሥት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ከኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ተጽእኖዎች ነፃ የመሆን መብት አለው፡፡

2/ ባለፈቃዱ የኤዲቶሪያል ነፃነቱ የተጠበቀ ነው፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ ነው፡፡

3/ በሕግ በግልፅ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በባለፈቃዱ የብሮድካስት ስርጭት ላይ የይዘት ግዴታዎች አይጣሉም፡፡

4/ ባለፈቃዱ የፕሮግራም ቻናሎችን የመምረጥ፣ የመቀበልና የማሰራጨት እንዲሁም ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን የመጠቀም መብት አለው፡፡

5/ ባለፈቃዱ ሕገ-መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሰራር ከተፈፀመበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

6/ ባለፈቃዱ በመረጠው ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አለው፡፡

7/ ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት ፈቃድ፣ የተጨማሪ ቻናል ፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት የማግኘት መብት አለው፡፡

8/ ባለስልጣኑ ለባለፈቃዱ መብቶች ተግባራዊነት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## 20. *ፕሮግራም፣ ዜና እና ማስታወቂያን በሕግ አግባብ የማሰራጨት ግዴታ*

ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም፣ ዜና ወይም ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

1/ ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን፣ የማስታወቂያ አዋጁን፣ የሙያውን የስነ-ምግባር መመሪያ፣ ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ የወጡ ሕግጋትን እና ሌሎች የአገሪቱን ሕጎች በማክበር መሰራጨት ይኖርበታል፤

2/ ለደንበኞቹ የሚያቀርባቸው የብሮድካስት አገልግሎት ቻናሎች ለደንበኞች ከማቅረቡ በፊት ሕግን የሚያከብሩ፣ የሕብረተሰቡን ባህልና ጥቅም የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

3/ የማንኛውንም ሰው የግል ሕይወት የመከበር መብትን የሚጥስ፣ የሰው ልጆችን ክብር የሚፃረር፣ ለጤናና ለደኅንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የሚያበረታታ፣ የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም፣ ጦርነትን የሚቀሰቅስ፣ ሰላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ የሚቀሰቅስ፣ የሰው ዘርን፣ ቋንቋን፣ ዜግነትን፣ ብሔርን፣ ቀለምን፣ ኃይማኖትን፣ ሥርአተ ጾታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ ህመምንና የአካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅስ መሆን የለበትም፤

4/ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጥቃት ወይም ሌላ አሰቃቂ ወይም አስደንጋጭ ሁኔታዎችን የሚዘግቡ ዜና ወይም ፕሮግራሞች ሲሠራጩ በአቀራረባቸው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5/ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን አመለካከትና ስነልቦና ሊጎዳ የሚችል ፕሮግራምን ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ማሰራጨት የለበትም፡፡

6/ ፕሮግራሞች የሚቀርቡት በውጭ ሀገር የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪ በኩል በሚሆንበት ጊዜ ከአቅም በላይ የሆነ የቴክኒክ ተግዳሮት ከሌለ በስተቀር በሚያሰራጫቸው ቻናሎች ውስጥ የሚሰራጩ ማናቸውም ማስታወቂያዎች የሀገሪቱን ህግ ያከበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

7/ በውጭ አገር ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የፕሮግራም ቻናሎች ውስጥ በሀገር ውስጥ የተዘጋጁ ማስታወቂያዎችን ማካተት የለበትም፡፡

8/ በሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ኃይማኖት ወይም እምነት ማንኳሰስ፣ ወይም በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀሰቅስ የለበትም፡፡

9/ ከስፖርታዊ ውድድር ጨዋታ ጋር በተያያዘ በልዩ ሁኔታ ጨዋታው በሚተላለፍበት ቻናል ብቻ የፕሮግራሙ ባለቤት ወይም የጨዋታው ስፖንሰር ድርጅት ማስታወቂያ ወይም የስፖንሰርሽፕ መግለጫ ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት፣ በጨዋታው አካፋይ እና መጨረሻ ለማስተዋወቅ ይችላል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (9) የተደነገገው ቢኖርም፣ የውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪውን እና የአጋሮቹን አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ካልሆነ በስተቀር በሀገር ውስጥ የተዘጋጁ ፕሮግራሞችን ከማስታወቂያ ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ ለማዋል በውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪ ቻናል መተላለፍ የለበትም፡፡

## *21. የባለፈቃዱ አስተዳደራዊ ግዴታዎች*

ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት አስተዳደራዊ ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1/ ለደንበኞች የሚያደርሳቸውን የፕሮግራም ቻናሎች ብዛትና ቋንቋ፣ የእያንዳንዱን ቻናል ስም፣ የይዘት አይነትና ትኩረት፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የፕሮግራም ቻናሎቹ የተዘጋጁበትን አገር፣ የቻናሎቹን አቅራቢ ባለቤት ስምና አድራሻ እና የገንዘብ ምንጭ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፡፡

2/ የሚያቀርባቸው የፕሮግራም ቻናሎች ከህጋዊ የፕሮግራም ባለቤቶች አስቀድሞ ስምምነት ወይም ፈቃድ የተገኘባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

3/ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ከይዘት ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረቶች ማድረግ ይኖርበታል፤

(ሀ) ፕሮግራሞች የሀገሪቱን ህጎች፤ የህብረተሰቡን ሞራል እና ባህል እና ጥቅም የማይቃረኑ መሆኑን እና ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ መደረጉን፤

(ለ) ፕሮግራሞች የማንኛውንም ሰው የግል ህይወት የመከበር መብት የማይጥሱ፣ የሰው ልጅ ክብርን የማይጻረሩ፣ ለጤናና ለደህንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የማያበረታቱ፤ የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም እና ሰላምና ጸጥታ እንዲደፈርስ የማይቀሰቅሱ፤ ዘርን፣ ቋንቋን፣ ዜግነትን፣ ቀለምን፣ ሀይማኖትን፣ ስርዓተ-ጾታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ ህመምንና አካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅሱ እንዳይሆኑ፤

4/ ለደንበኞች በሚያቀርባቸው የፕሮግራም ቻናሎች ውስጥ ቢያንስ ሦስት የአገር ውስጥ የሕዝብ፣ የማህበረሰብና የንግድ ቻናሎችን ወይም የሕፃናት ፕሮግራሞችን ማካተት፡፡

5/ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ ተመን እንዲሁም ማናቸውንም የክፍያ ተመኑን ለውጥ ዝርዝር ለባለስልጣኑ በየጊዜው ማሳወቅ፡፡

6/ ለደንበኞች የሚያቀርባቸውን ፕሮግራሞች ለባለስልጣኑ ያለክፍያ ማቅረብ፤ ባለፈቃዱ በራሱ ያዘጋጃቸውን ፕሮግራሞች ያለማሰራጨት፤

7/ ፈቃድ ባወጣበት የአገልግሎት ዓይነት ብቻ አገልግሎቱን ማቅረብ፡፡

8/ ለባለስልጣኑ ክትትል እና ቁጥጥር ያመች ዘንድ የሥራ ቦታውን እና ለሥራው የሚጠቀምባቸውን መሣሪያዎች በተጠየቀ ጊዜ ማሳየት፡፡

9/ የደንበኞቹን ቁጥር ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፡፡

10/ የደንበኞችን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥያቄ፣ የቴክኒክ፣ የክፍያና መሰል ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣ የጥሪ ማዕከል ማቋቋም ወይም ማመቻቸት፡፡

11/ በመርሀ-ግብሩ መሰረት ፕሮግራሞችን ማሠራጨት፤ በመርሀ ግብሩ መሠረት ማሠራጨት ካልተቻለ አስቀድሞ ማሳወቅ፡፡

12/ የብሮድካስት መሳሪያዎችን ከውጭ ሀገር የሚያስመጣ ከሆነ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማረጋገጫ ሠርተፍኬት ማግኘት፤

13/ ባለፈቃዱ በሀገር ውስጥ የሚቀጥራቸው ባለሙያዎች የውጭ አገር ዜጐች ከሆኑ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል የስራ ፈቃድ ያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ፤

14/ የገቢ ምንጩ ከደንበኞች የሚሰባሰብ የአገልግሎት ክፍያ ወይም ከኮሚሽን ወይም ከመሰል ክፍያ በመሆኑ ገቢውን ከማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ ሽያጭ ማድረግ የለበትም፡፡

15/ የድርጅቱን ስራ አስኪያጅ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

16/ ባለፈቃዱ የሚያቀርበው አገልግሎት ተጠቃሚው ለራሱና ለቤተሰቡ ተስማሚ ናቸው ብለው ያሰቡትን ይዘት እንዲወስኑ የሚያስችል የወላጅ ቁጥጥር ዘዴዎች ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

17/ እንደአስፈላጊነቱና እንደቴክኒክ አቅሙ ማስታወቂያንና ዜናን ጨምሮ ያሰራጨውን ማናቸውም ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ፡፡ በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበም ቅሬታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ፕሮግራሙን ይዞ ማቆየትና በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው አካል ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር ሲጠየቅም ቅጂውን በራሱ ወጪ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

18/ ባለሥልጣኑ በውጭ ሀገር የሚዘጋጁ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች የዚህን አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(3)ን እና የዚህን መመሪያ አንቀጽ 20ን የሚጥሱ ወይም ሌሎች ፕሮግራሞች የሀገርን ደህንነት ወይም የህዝብ ጥቅምን አደጋ ላይ የሚጥሉ መሆናቸውን ካወቀ ለባለፈቃዱ በማሳወቅ ባለፈቃዱ ወዲያውኑ ጥሰቱ እንዲስተካከል የውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪውን በማነጋገር ከ7 ተከታታይ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥሰቱን ለማስተካከል የተወሰዱ እርምጃዎችን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ያሳውቃል፡፡

19/ ለሚጠቀምባቸው አገልግሎቶች ከሀገር ውጭ የሚዲያ መሳሪያዎችን የሚያስመጣ ከሆነ መሳሪያዎቹ ስታንዳርድ እና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡

20/ ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ ፈቃድ ይህን አገልግሎት ብቻ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በሌላ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ለመሰማራት ከፈለገ ወይም ባለፈቃዱ ራሱ ያዘጋጀውን ይዘት የሚያሰራጭ ከሆነ ተገቢውን ፈቃድ ከባለሥልጣኑ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## *22. ለውጦችን ስለማሳወቅና ስለማስፈቀድ*

1/ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመር፤

ለ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲቋረጥ፤

ሐ) የፕሮግራም ቻናል ለውጥ ሲያደርግ፤

መ) የሥራ አድራሻውን ወይም የድርጅቱን ስም እና አድራሻ ሲለውጥ፤

ሠ) የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ሲለውጥ፤

ረ) ፈቃድ ለመውሰድ ባቀረባቸው ሌሎች መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደርግ፣

2/ ባለሥልጣኑ የተደረገው ለውጥ በሕግ አግባብ መከናወኑን ይገመግማል፡፡

3/ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ከማድረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የማሰራጫ መሳሪያ ካለው ለመለወጥ ሲፈልግ፡፡

ለ) ከውጭ አገር ብሮድካስተሮች ወይም የፕሮግራም ቻናሉ ሕጋዊ ባለቤቶች ጋር ያደረገውን ውል ለማሻሻል ወይም ለማቋረጥ ሲፈልግ፣

ሐ) ከብሮድካስት ኔት ወርክ ወይም ከሳተላይት ድርጅቶች ጋር ያደረገው ውል ወይም ስምምነት ካለው ሲያሻሽል፣ ወይም ሲያቋርጥ፣ ወይም ፈቃድ ካገኘበት ሳተላይት ውጪ በሌላ ሳተላይት የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ለማሰራጨት ሲፈልግ፡፡

መ) የድርጅቱን የአክስዮን ባለድርሻዎች የአክስዮን ድርሻ መጠን ለመጨመር፣ ለመቀነስ፣ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ፣ ሌላ የመገናኛ ብዙሃን የንግድ ማኅበርን ለመግዛት፣ ለመዋሀድ ወይም መሰል ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ፡፡

## 23. የተጨማሪ የፕሮግራም ቻናል ዕውቅና

1/ ፈቃድ ከወጣበት ቻናል ውጪ ተጨማሪ ቻናል ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ወይም አዲስ ቻናሎችን ያካተተ ባለፈቃድ ለተጨማሪው ቻናል ከባለስልጣኑ ዕውቅና ማግኘት አለበት፡፡

2/ ባለፈቃዱ ተጨማሪ የቻናል ጥያቄውን በባለስልጣኑ በተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መረጃዎች ከተጨማሪ የቻናል ጥያቄው ጋር በማያያዝ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ) በአገልግሎቱ ሊተላለፉ የታቀዱትን ወይም አዲስ ያካተታቸውን ተጨማሪ የፕሮግራም ቻናሎች ብዛትና ቋንቋ፣

ለ) የእያንዳንዱን ቻናል ስም፣ የይዘት አይነትና ትኩረት፣ አላማ

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የፕሮግራም ቻናሎቹ የተዘጋጁበትን ሀገር፣ የቻናሎቹን አቅራቢ ባለቤት ስምና አድራሻ ማስረጃ፣

4/ ባለስልጣኑ ተጨማሪ የቻናል ጥያቄውን በመገምገም ከተቀበለው ለቻናሉ የተተመነውን ክፍያ በማስከፈል ዕውቅና ይሰጣል፡፡

5/ ባለስልጣኑ የቀረበውን የተጨማሪ ቻናል ጥያቄ ካልተቀበለው ምክንያቱን፣ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለባለፈቃዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 24. *አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ስለማቅረብ*

1/ ባለፈቃዱ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴና ሠራተኞች፣ ዓመታዊ የበጀት እቅድ፣ የሂሣብ መዝገብ፣ ዓመታዊ የስራና የሒሳብ ሪፖርት በተመለከተ መረጃ መያዝ፣ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ሪፖርቶች የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሀ) የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣

ለ) የድርጅቱን የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ፣ ዓመታዊ የወጪና ገቢ ሪፖርት እና የኦዲት ሪፖርት፣

ሐ) የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች ብዛት፣

3/ ባለፈቃዱ ከውጭ የተገኘን ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ከውጭ አገር በእርዳታ ወይም በስጦታ መልክ ከመቀበሉ በፊት በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ማስፈቀድ አለበት፡፡

4/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን መረጃና ሪፖርት በአግባቡና በጥንቃቄ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

## 25. *ጥቆማ፣ ቅሬታንና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ*

1/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከደንበኞች የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ ለሚቀርብለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር በተያያዘ በማናቸውም ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ከተወሰነበት የአቤቱታውን ብዛት፣ ምክንያት፣ የተሰጠውን ውሳኔና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዶች የራሳቸውን የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ተከትለው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

## 26. *የአገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል*

1/ ባለፈቃዱ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መሰረት የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ፣ የፈቃድ ክፍያ፣ አመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል፡፡

ሀ) የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያው፣ አመልካቹ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ሲያቀርብ ይከፍላል፡፡

ለ) የፈቃድ ክፍያው፣ አመልካቹ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት ይከፍላል፡፡

ሐ) ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ይከፍላል፡፡

2/ ባለፈቃዱ የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን ካልከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚፈለግበትን አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን አጠቃሎ ከከፈለ ባለስልጣኑ መቀጫውን ሊያነሳለት ይችላል፡፡

4/ የክፍያው መጠን በመንግስት በሚጸድቀው ተመን መሰረት የሚወሰን ሲሆን ክፍያው በባለስልጣኑ በየጊዜው እየተጠና በመንግስት ይወሰናል፡፡

## 27. ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡት ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፡፡

2/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደ ሚያደርግበት ሥፍራ ለመግባት የመታወቂያ ወረቀቱን እና ከባለሥልጣኑ ቁጥጥር እንዲያደርግ የተጻፈለትን ደብዳቤ በመያዝ በባለፈቃዱ የስራ ቦታ በስራ ሰአት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡

3/ ለክትትል እና ቁጥጥር ያመች ዘንድ ባለፈቃዱ አገልግሎት መስጫ የሥራ ቦታውን ክፍት ያደርጋል፣ በኢንስፔክተሩ የሚጠየቀውን የሰነድ ቅጅም ያቀርባል፡፡

4/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ሲያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዱ መታደሱን፣ አመታዊ ክፍያ መክፈሉን አግባብ ያላቸውን ሰነዶችና የፕሮግራም ቅጅዎች መያዛቸውን፣ የአዋጁና የመመሪው ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማየትና ቅጅ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## 28. ፈቃድ ስለማስተላለፍ

1/ ባለፈቃዱ ሥራውን ማካሄድ ካልቻለ ፈቃዱን በመመለስ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ሲፈቀድለት መሣሪያውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2/ ፈቃዱን ለማስተላለፍ የድርጅቱን የአክስዮን ባለድርሻዎች የአክስዮን ድርሻ መጠን ለመጨመር፣ ለመቀነስ፣ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ፣ ሌላ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅትን ወይም አክስዮንን ለመግዛት፣ ለመዋሀድ ወይም መሰል ለውጥ ለማድረግ ወይም ከባለቤትነት ለውጥ ጋር የተያያዙ ውሎችን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ወይም ለመሰረዝ የሚፈልግ ባለፈቃድ በቅድሚያ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከትና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ አስቀድሞ ከባለሥልጣኑ በፅሁፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር፡-

ሀ) ፈቃዱን ማከራየት፣ በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤

ለ) የፈቃድ አይነትን መለወጥ፤ አክስዮንን ማስተላለፍ፤

ሐ) በፈቃዱ የተሠጡትን መብቶችና የፈቃድ ሁኔታው ላይ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

4/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱ እንዲተላለፍ የሚፈቅደው ፈቃድ የሚተላለፍለት ድርጅት የሚከተሉትን ሲያሟላ ይሆናል፡-

ሀ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው የፈቃድ ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት፣ ነባር ደንበኞችን በብቃት ለማገልገል የሚያስችል በቂ የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ያለው ከሆነ፤ እና

ለ) የፈቃዱ መተላለፍ ከባለቤትነት ቁጥጥር ህግ ጋር በተያያዘ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን የማይተላለፍ ከሆነ ነው፡፡

5/ በአዋጁና በመመሪያው የተደነገጉት መብትና ግዴታዎች ፈቃዱ ለተላለፈለት ሰው አብረው ይተላለፋሉ፡፡

## ***ክፍል አራት***
## ***ስለአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎች***

### 29. ***አስተዳደራዊ እርምጃዎች***

1/ ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁንና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት ባለስልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤

ሐ) ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፤

መ) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፤

2/ ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሲወስን፡-

ሀ) ባለፈቃዱ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊጣልበት እንደሆነና ጥፏል የተባለውን ጉዳይ እንዲያውቅ ማድረግና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፤

ለ) እርምጃው የሚወሰድበትን ምክንያት፣ የማስተካከያ እርምጃውን፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ገደብ በፅሁፍ ለባለፈቃዱ ማሳወቅና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) የባለፈቃዱን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪዎችን የማክበር እና ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ፕሮግራሙ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ጊዜ ውስጥ በፕሮግራሙ ላይ ምርመራ ካልተጀመረ አስተዳደራዊ እርምጃው በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 30. አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ስልጣን እና ይግባኝ አቀራረብ

1/ የፈቃድ እድሳትን የመከልከል፣ ፈቃድን የማገድ እና የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

2/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የገንዘብ ቅጣት የመጣል እና አንድን ፕሮግራም የማገድ ወይም የመሠረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3/ ባለሥልጣኑ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4/ ቦርዱ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

5/ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 31. በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች

ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት በፍርድ ቤት የሚከተሉት ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላሉ፡-

1/ የስም ማጥፋት ተግባር በመገናኛ ብዙሀን ሲፈፀም በፍትሐብሔር ሀላፊነት እስከ 300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ሊያስቀጣ ይችላል፡፡

2/ ዓቃቤ ሕጉ በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ወይም ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ውሳኔ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

4/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 32. የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍሉ ተግባርና ሃላፊነት

1/ የፈቃድና ምዝገባ ሥራዎች የሚከናወኑት በባለሥልጣኑ ውስጥ በተቋቋመ መደበኛ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ነው፡፡

2/ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍሉ፡-

ሀ) ፈቃድ ጠያቂ አመልካቾች ሞልተው የሚያቀርቡትን የማመልከቻ ቅጽና አባሪ ሰነዶች ይቀበላል፣ ይመዘግባል፣ ለዚሁም ማስረጃ ይሰጣል፤

ለ) የመዘገባቸውን አመልካቾች ዝርዝር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አመቺ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ስለአመልካቾች ከህዝብ አስተያየት ይሰበስባል፤

ሐ) መዝግቦ የተቀበላቸውን የማመልከቻ ቅጾችና አባሪ ሰነዶች እንደዚሁም የሕዝብ አስተያየቶች በአግባቡ ይይዛል፤

መ) በዚህ መመሪያ በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት ዝርዝር ማጣራት በማድረግና በመገምገም ከአስፈላጊ ማብራሪያ ጋር የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ሃላፊ ያቀርባል፤

ሠ) መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉና በቀጥታ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የብሮድካስት አገልግሎት ሠጪውን ስም፣ አድራሻ፤ የፖስታና የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና

የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የጣቢያውን ስራ አስኪያጅና ተወካዮች ስምና ስልክ ቁጥር በማጠናቀርና በመመዝገብ በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፡-

ረ) ሌሎች ተያያዥ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## 33. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

1/ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁ እና ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሕግ መሰረት የተሰጠ ፕሮግራሞችን ለደንበኞች በክፍያ የማቅረብ አገልግሎት ፈቃድ እንደፀና የሚቆይ ሲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱ በአዋጁ አንቀፅ 44 እና 88 መሠረት ባለፈቃዶች አደረጃጀታቸውን በማሻሻል ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን ለማሻሻል ሲወስን የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለፈቃዱ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የማሻሻያውን ዝርዝር፤

ለ) ለማሻሻል ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፤ እና

ሐ) ማሻሻያው ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ፡፡

## 34. *የተሻረ መመሪያ*

1/ የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 04/2001 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ትእዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 35. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

2/ ባለሥልጣኑ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ በቦርዱ የፀደቁ መመሪያዎችንም አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 36. *መመሪያው የፀና ስለመሆኑ*

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ከጸደቀና በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

*የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ቦርድ*